# የብቁነት ስብሰባ፡ የቤተሰብ/የአሳዳጊ አጠቃላይ እይታ

የተማሪ ስም፦ ቀን፦

**የብቁነት ኮሚቴ ምንድነው?**
የብቁነት ኮሚቴው ልጅዎ በትምህርት ቤት ውስጥ መማርን የሚደግፉ የልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች የሚያስፈልገው አካል ጉዳተኛ መሆኑን ለመወሰን አንድ ላይ የሚሰበሰብ ቡድን ነው።

**የብቁነት ኮሚቴ አካል የሆነው ማነው?**
ይህ ቡዱን የትምህርት ቤት ሰራተኞች እና እርስዎ ማለትም ወላጁ ወይም አሳዳጊው ሁለቱንም ያካትታል። አባላቶቹ ብዙውንጊዜ የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

- እርስዎ (ወላጁ ወይም አሳዳጊው)
- የትምህርት ቤት አስተዳዳሪ (እንደ ርእሰ መምህር ወይም ረዳት ርእሰመምህር ያሉ) - ብዙ ጊዜ "LEA" (የአከባቢ ትምህርት ኤጀንሲ ተወካይ) በመባል ይታወቃሉ
- የአጠቃላይ ትምህርት መምህር (እንደ የልጅዎ ክፍል መምህር)
- የልዩ ትምህርት መምህር
- የተማሪ ድጋፍ አስተባባሪ (SSC)
- የትምህርት ቤት ነርስ
- የትምህርት ቤት የስነ ልቦና ባለሙያ
- የትምህርት ቤት ማህበራዊ ሰራተኛ
- ማንኛውም የተዛማጅ አገልግሎት ሰጪዎች (እንደ የንግግር ቴራፒስት ወይም የኦኪፔሽናል ቴራፒስት)
- በእርስዎ ወይም በትምህርት ቤቱ የተጋበዙ ሌሎች ሰዎች

**በስብሰባው ወቅት ምን ይከሰታል?**

- ቡድኑ ከተለያዩ ምንጮች የተገኘውን መረጃዎች እንደ የእርስዎን ግብአት፣ የአስተማሪ አስተያየት፣ ምልከታ እና ማንኛውንም የተደረጉ ፈተናዎችን ወይም ግምገማዎችን ያካተተ ግምት ውስጥ ያስገባል። ለልጅዎ የብቃት ስብሰባ ግምገማን ያጠናቀቀ እያንዳንዱ ሰው ግኝታቸውን ይገመግማል እና ያጠቃልላል።
- ቡድኑ አንድ ላይ ልጅዎ የልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች የሚያስፈልገው "አካል ጉዳተኛ ልጅ" ብቁ ስለመሆኑ ይነጋገራል።

**ምን ዓይነት ውሳኔዎች ተደርገዋል?**

- ቡድኑ አንድ ወይም ከዛ በላይ አካል ጉዳተኝነት መኖራቸውን እና የአካል ጉዳቱ/ጉዳቶቹ ሁኔታ ለማወቅ <u>የብቁነት ቅጾችን</u> ይጠቀማል። ያለው መረጃ የአካል ጉዳት መኖሩን የሚያመለክት ከሆነ ልጅዎን ብቁ ሆኖ እንዲያገኝ ፈቃድዎ ይጠየቃል።
- ቡድኑ ብቁነትን ሲወስን መግባባት ላይ ለመድረስ ይጥራል። እያንዳንዱ የቡድን አባል በውሳኔው መስማማቱን ወይም አለመስማማቱን ያጋራል።

የብቁነት ቅጾችን ለማየት ባርኮዱን ስካን ያድርጉ

**በብቁነት ስብሰባ ወቅት እንደ ወላጅ/አሳዳጊ ያለኝ ሚና ምንድን ነው?**

- በስብሰባው ወቅት ውይይቱ ላይ ንቁ ተሳትፎ ያድርጉ። ማስታወሻ: ለመሳተፍ የቋንቋ ትርጉም እና/ወይም የ*ADA* መስተንግዶ ከፈለጉ ትምህርት ቤቱን ያሳውቁ።
- ሃሳቦችዎን፣ አመለካከቶችዎን እና የሚኖሮዎትን ማንኛውንም ስጋት ለማካፈል አያመንቱ።
- እንደየ አስፈላጊነቱ ጥያቄዎችን እና ማብራሪያ ይጠይቁ።
- በብቁነት ውሳኔው ላይ መስማማትዎን ወይም አለመስማማትዎን ለመግለጽ ያስቡበት።
- ስለ ስብሰባው ውጤት የሚያሳስብዎት ነገር ካለ ቡድኑን ስለሚቀጥሉት እርምጃዎች መጠየቅ ይችላሉ፣ ይህም አለመግባባቶችን ለመፍታት አማራጮችን ሊያካትት ይችላል። እንዲሁም ለተጨማሪ መረጃ *PRC*ን ማግኘት ይችላሉ።

## ለብቁነት ስብሰባ መዘጋጀት

የበለጠ ዝግጁነት እና በራስ የመተማመን ስሜት እንዲሰማዎት የሚከተሉት ነገሮችን ማድረግ ይችላሉ፦

- ☑ የወላጅ ትረካ ለመጻፍ ያስቡበት እና ቡድኑ እንዲያስብበት አስቀድመው ያስገቡት። (የወላጅ የመረጃ ማእከል (PRC) ከእርስዎ ጋር ሊያጋሯቸው የሚችሉ የወላጅ ትረካዎች ናሙና አልዋቸው።)
- ☑ ማጋራት የሚፈልጓቸውን ማናቸውንም የግል ሪፖርቶች (ግምገማዎች፣ የህክምና ሪፖርቶች) ያሰባስቡ እና ከስብሰባው በፊት ያቅርቡ።
- ☑ ቡዱኑ ግምት ውስጥ ያስገባው የአካል ጉዳት ምድብ ለመለየት የብቁነት ቅጾችን ይገምግሙ።
- ☑ የብቁነት ፓኬጅ ከፈተና ክፍሎች ጋር ከብቁነት ስብሰባው ቢያንስ ሁለት ቀናት በፊት ይገኛል። ከስብሰባው ቢያንስ ከሁለት ሳምንታት በፊት ፓኬጁን ከትምህርት ቤትዎ ልዩ ትምህርት አስተዳደር ረዳት ጋር ለመቀበል ዕቅዶችን ያረጋግጡ። በቻይልድ ፋይንድ ፕሮግራም የሚገመገሙ ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች ወደ Child Find በ 703.228.2700 መደወል አለባቸው።
- ☑ የብቁነት ፓኬጁን ከሁሉም የግምገማ ክፍሎች ጋር በጥንቃቄ ለመገምገም ጊዜ ይስጡት።
- ☑ ከዚህ በታች ባለው "የመነጋገርያ ነጥቦች" ክፍል ውስጥ ለማካፈል የሚፈልጉትን ማንኛውንም አስተያየት/ማስታወሻ ይጻፉ።
- ☑ በስብሰባው ወቅት መጠየቅ የሚፈልጉትን ጥያቄዎች ከታች "ጥያቄዎች" የሚለው ክፍል ላይ ይጻፉት።
- ☑ ስለ ልዩ ትምህርት ሂደት የበለጠ ለማወቅ PRCን ያግኙ። ከቻሉ፣ "የልዩ ትምህርት መግቢያ እና የተማሪ ድጋፍ ሂደት" ክፍለ ጊዜያቸውን ለመከታተል ይሞክሩ ወይም አሁን በመስመር ላይ ይመልከቱት! ጠቃሚ መረጃ ለማግኘት ጥሩ መንገድ ነው።
- ☑ አንድን ሰው (እንደ ጓደኛ፣ ጠበቃ ወይም የቤተሰብ አባል) ከእርስዎ ጋር ወደ ስብሰባው ለማምጣት ካሰቡ ቦታ እና ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት እንዲችል ትምህርት ቤትዎን አስቀድመው ያሳውቁ።

የPRC የመስመር ላይ ቪዲዮ ሞጁሎች

WATCH NOW

| ሊታሰብባቸው የሚገባ ጥያቄዎች | የመነጋገሪያ ነጥቦች/ተጨማሪ ጥያቄዎች |
|---|---|
| • ቀጣይ እርምጃዎች ምንድናቸው?<br>• ልጄ ብቁ ሆኖ ከተገኘ፣ ለተናጠ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ማነጋገር ያለብኝ ማንን ነው?<br>• በስብሰባው ወቅት ስለተደረገው ውሳኔ ሰነድ መቼ ነው የምቀበለው?<br>• ዛሬ በተደረገው ስብሰባ ውጤት ካልተስማማሁ ምን ማድረግ አለብኝ?<br>• ልጄን ብቁ ለመሆን መስማማቴን ለመወሰን ተጨማሪ ጊዜ ካስፈለገኝ ምን ማድረግ እንችላለን? | |

LEARN MORE

እርስዎ ለመርዳት PRC እዚህ ይገኛል። 703.228.7239 ላይ ይደውሉልን ወይም prc@apsva.us ኢሜል ይላኩልን።

PEATC:- ጠቃሚ የወላጅ መብቶች

የVDOE የብቁነት ቪድዮ

PEATC:- ምዘናዎችን መረዳት

PEATC: ቤል ከርቭ እና ደረጃውን የጠበቀ ፈተና

PEATC: የብቁነት እውነታ ሉህ

የVDOE የልዩ ትምህርት የቤተሰብ መመሪያ